# የዕጽዋት አዳቃይ መብት መመሪያ ቁጥር 769/2013

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

በግብርና ሚኒስቴር የወጣ መመሪያ ቁጥር 769/2013

የግብርና ሚኒስቴር በዕፅዋት አዳቃይ መብት የወጣ አዋጅ ቁጥር 1068/2010 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የዕፅዋት አዳቃይ መብት መመሪያ ቁጥር 769/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **የዕጽዋት አዳቃይ መብት ተግባራዊ ስለማይሆንባቸው ሰብሎች ዝርዝር በተመለከተ**

ሚኒስቴሩ፤

1/ በአካባቢ፣በሰው፣በእንስሳት እና በዕጽዋት ብዝሃ ህይወት ጤንነትና ደህንነት አደጋ እንደሚያስከትሉ አግባብ ባለቸው ሌሎች ተቋማት በተደነገጉት የዕጽዋት ጀነራና ዓይነቴዎች ዝርዝር ተግባራዊ አያደርግም፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የዕጽዋት አዳቃይ መብት ተግባራዊ የማይደረግባቸው የዕጽዋት ጀነራና ዓይነቴዎችን ዝርዝር በተመለከተ የሚመለከታቸውን ተቋማት በተፈለገ ጊዜ ሁሉ መጠየቅና ማረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

3. **የዕጽዋት አዳቃይ መብት ማመልከቻ ስለሚቀርብበትና ስለሚመረመርበት ሁኔታ**

1/ ማንኛውም ሰው የዕጽዋት አዳቃይ መብት ለማግኘት በባለመብቱ ወይም በህጋዊ ወኪሉ የሚያቀርበው ማመልከቻ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፤

ሀ/ የባለመበቱ ስምና አድራሻ፤

ለ/ ማመልከቻው በወኪል የሚቀርብ ከሆነ የወኪሉ ስምና አድራሻ፤

ሐ/ ዝርያው ቤተሰብ የሆነበት የሰብል ዓይነቱ እና የተለምዶ ስያሜ፤

መ/ እጩ የዝርያው ስያሜ፤

ሠ/ የአደቃዩ የዕጩ ዝርያው መለያ ኮድ፤

ረ/ ዕጩ ዝርያውን ያዳቀለው ወይም አግኝቶ ያበለጸገው አዳቃይ ስም፤

ሸ/ ዝርያው የተዳቀለበት ወይም የጎለበተበት ሁኔታ አጭር ማብራርያ፤

ቀ/ የአገር ውስጥ ብዝሃ ሕይወት በመጠቀም ለጎለበተ ዝርያ የአርክቦተ ፈቃድ፤

በ/ ዝርያው ከኢትዮጵያ ውጭ የመብት ጥበቃ ያገኘ ከሆነ ያገኘበትን አገር ስም፤

ተ/ አገሪቱ በተቀበለቻቸው እና አባል በሆንችባቸው ዓለም አቀፍ እና አህጉር አቀፍ ስምምነት መሰረት ለአመልካቹ ልዩ መብት የሚያሰጥ መረጃ ካለው ማካተት፤

ቸ/ ዝርያው በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር በገበያ የቆየበት ጊዜ፤

ነ/ የዝርያው ዘር ስለመጠበቁ ቅድሚያ ስምምነት፤

ወ/ ማመልከቻው በምርምር ተቋም ወይም በአርሶ/አርብቶ አደር ወይም በማህበረሰብ ወይም በወከላቸው አካል የቀረበ ከሆነ የባለቤትነት መብት እንዲሰጠው የጠየቀበት ደብዳቤ ከሚኒስቴሩ የማመልከቻ ቅጽ ጋር ተያይዞ መቅረብ ይኖርበታል፤

2/ የዕጽዋት አዳቃይ መብት ማመልከቻ ከተገቢ የማመልከቻ ክፍያ ሰነዶች ጋር ከሚከተሉት በአንዱ ለሚኒስቴሩ ሊቀርብ ይችላል፤

ሀ/ በፖስታ፤

ለ/ ሚኒስቴሩ ለዚህ ተግባር ባዘጋጀው ኤሌክትሮኒክ ማመልከቻ፤

ሐ/ በፋክስ፤

መ/ አካል፤

3/ ሚኒስቴሩ የቀረበውን የዕጽዋት አዳቃይ መብት ማመልከቻ በሚከተሉት መንገዶች ማለትም

ሀ/ የቀረበው ማመልከቻ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት መሆኑን፤

ለ/ ከማመልከቻው ጋር አባሪ ሆነው የቀረቡ ማስረጃዎችን ትክክለኛ መሆናቸውን፤

ሐ/ በማመልከቻው የተገለጸው የዝርያ ባህርይ ሚኒስቴሩ ለማመሳከሪያነት ካዘጋጀው የሌሎች የተጠበቁ ዝርያዎች የባህርይ መገለጫ ሰነድ ጋር በማመሳከር የተለየ ስለ መሆኑን፤

ይመረምራል፤

መ/ የቀረበው የባህርይ መገለጫ ሰነድ በሚኒስቴሩ ተቀባይነት ካገኘ የባህርይ ፍተሻ ሙከራ እንዲካሄድ ይወስናል፤

ሠ/ እንደ አስፈላጊነቱም ሙከራውን ሳይካሄድ በአመልካቹ የቀረበው የዝርያ የባህርይ መገለጫ ሪፖርት በሚኒስቴሩ እውቅና ባለው ተቋም የተሰራ ከሆነ በቀጥታ ሊቀበል ይችላል፤

**4. የዝርያ ባህርይ መገለጫ ሰነድ እና አቀራረብ**

1/ የዝርያ ባህርይ መገለጫ ሰነድ እንደ የሰብሎቹ ዓይነት ሚኒስቴር መስርያ ቤቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባገኘ አሰራር ባሟላ መልኩ እና የሚከተሉትን የተክል ክፍሎች በዓይነት /Type/ ለመለየት የሚውሉትን ባህርያት በተናጠል ወይም በጥቅል በመዘርዘር ያዘጋጃል፤

ሀ/ ቅጠል፤

ለ/ የተክሉ የመራቢያ አካል፤

ሐ/ ግንዱ፤

መ/ ሥሩ፤

ሠ/ የአስተዳደግ ባሕርይው፤

ረ/ እንደ አስፈላጊነቱም ሌሎች ባህርያትን ማካተት ይቻላል፤

2/ የተክል ባህርያት መገለጫ ሰነድ በዓይነት፣ በመጠን እና በዓይነት መሰል ባህርያት ተዘርዝሮና ተዘጋጅቶ ለተገልጋዮች ተደራሽ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

**5. የአርሶ/አርብቶ አደር እና የማህበረሰብ ዝርያዎች የአዳቃይ መብት አሰጣጥ በሚከተለው መልኩ ተፋጻሚ ይሆናል፤**

1/ የአርሶ/አርብቶ አደር እና የማህበረሰብ ዝርያዎች የአዳቃይ መብት ጥበቃ ለማግኘት የሰብል ዓይነቴው በአገሪቱ የብዝሃ ሕይወት ተቋም

ሀ/ መገኛው ወይም ምንጩ /center of origin/ የኢትዮጵያ ስለመሆኑ፤ ወይም

ለ/ በብዝሃ ሕይወት ተለያይነት /center of diversity/ ዝርዝር ውስጥ የተገለጸ ሲሆን ነው፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ፊደል ተራ ሀ እና ለ ከተገለጹት ውጭ አርሶ/አርብቶ አደሮች በተናጠል ወይም በጋራ እንደ ማህበረሰብ የአዳቃይ መብት እንዲጠሰጣቸው ሲፈልጉ በአዋጁ አንቀጽ 4 መሰረት መብታቸውን ከመጠቀም አይከለከሉም፡፡

**6. ማንኛውም አመልካች እንደ አርሶ/አርብቶ አደር ወይም እንደ ማህበረሰብ የዝርያ የባለቤትነት መብት ለማግኘት የማመልከቻ አቀራረብና ዳሰሳ ጥናት ሂደት በሚከተለው መልኩ ተፈጻሚ ይሆናል፤**

1/ የመጀመሪያ ደረጃ ማመልከቻውን ለቀበሌ የግብርና መዋቅር ያቀርባል፤

2/ ማመልከቻውን ሲያቀርብ ዝርያው ከሌሎች ዝርያዎች የሚለይበትን ልዩ የባሕርይ መገለጫ እና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎችን በዚህ መመሪያ በአዝል ተያይዞ በቀረበው ቅጽ መሰረት ሞልቶ ያቀርባል፤

3/ የቀበሌ የግብርና መዋቅር የቀረበለትን ማመልከቻ መሰረት በማድረግ የባለቤትነት መብት ጥያቄ በቀረበበት ዕጩ የአካባቢ ዝርያ ላይ ቀበሌ አቀፍ ቅኝት በማካሄድ ተቃወሞ አለመኖሩን በማረጋገጥ የድጋፍ ደብዳቤውን ይጽፍለታል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ን/አንቀጽ 3 የወረዳ የግብርና መዋቅር የቀረበለትን የቀበሌ የድጋፍ ደብዳቤ መሰረት በማድረግ ወረዳ አቀፍ ቅኝት ያካሂዳል፤ተቃወሞ አለመኖሩን በማረጋገጥም የድጋፍ ደብዳቤውን ለዞን ወይም ለክልሉ የግብርና መዋቅር ይልካል፤

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የክልል ግብርና ቢሮ በስሩ የዘር ጥራት ተቆጣጣሪ መዋቅር ካለው በዚህ መዋቅር ከሌለው ግን የሰብል ልማትን በሚመለከተው ክፍል አማካይነት ዝርያው በሌሎች ዞኖች አለመኖሩን አጣርቶ ማስረጃዎችን ከማመልከቻው ጋር በማያያዝ ለግብርና ሚኒስቴር ይልካል፤

6/ የግብርና ሚኒስቴር በዚህ አንቀጽ ን/አንቀጽ 5 መሰረት የደረሰውን ማመልከቻና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎች መሰረት በማድረግ

   ሀ/ የአገሪቱ የብዝሃ ሀይወት ተቋም ስለ ዕጩው የአካባቢ ዝርያ የይሁንታ አስተያየት እንዲሰጠው ይጠይቃል፤

   ለ/ የአገሪቱ የብዝሃ ሕይወት ተቋም ሪፖርት ሲደርሰው ሚኒስቴሩ ስለቀረበው ዕጩ ዝርያ ተቃወሞ ስለአለመኖሩ ሰፊ ሽፋን ባለው መገናኛ ብዙሃን ጥሪ ያደርጋል፤ማስታወቂያው የሚቆይበትን ጊዜ በማስታወቂያው ይገለጻል፤

   ሐ/ በማስታወቂያው በተገለጸው የጊዜ ገደብ ውስጥ መቃወሚያ ካልቀረበ ሚኒስቴሩ በቀረበው ዕጩ የአከባቢ ዝርያ ላይ የባሕርይ ፍተሻ ሙከራ እንዲካሄድ ያደርጋል፤

7/ ሚኒስቴሩ የአርሶ/አርብቶ አደር እና የማህበረሰብ ዝርያዎች የባሕርይ ፍተሻ ተግባርን

   ሀ/ በራሱ የባሕርይ ፍተሻ ጣቢያ ላይ፤ወይም

   ለ/ ውክልና በሚሰጣቸው እና በየአካባቢው በሚገኙ የምርምር ማዕከላት ወይም ዩኒቨርስቲዎች ተፈጻሚ ሊያደርግ ይችላል፤

8/ የባህርይ ፍተሻ የሙከራ ማሳ ዲዛይን እና የናሙና መጠን አወሳሰድ ሚኒስቴሩ ለየሰብሎቹ በሚያዘጋጀው የባህርይ ፍተሻ ፕሮቶኮል መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

9/ የአርሶ/አርብቶ/ማህበረስብ ዝርያ የወጥነት ደረጃ በኢትዮጵያ ደረጃዎች ኤጀንሲ ለጥራቱ ለተገለጸ ዘር በወጣው የዝርያ ጥራት ለዝቅተኛው የዘር ደረጃ በተፈቀደው የኦፍ ታይፕ መጠን መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤

10/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 9 መሰረት ዝርያው ብቁ ሆኖ ከተገኘ እና ተቃዋሚ ካልቀረበ የአዳቃይ መብቱ ለአመልካቹ ይሰጠዋል፤

7. **ለመንግስት የምርምር ተቋም የዕጽዋት አዳቃይ መብት አሰጣጥ በሚከተለው መልኩ ተፈጻሚ ይሆናል፤**

የባሕርይ ፍተሻ መስፈርቶችን አሟልቶ ለመብት ጥበቃ ዝግጁ የሆነን ዝርያ ለመንግሰት የምርምር ተቋም የባለቤትነት መብት ለመስጠት መሟላት ያለባቸው መስፈርቶች፤

1/ የዕጽዋት ዝርያ መብት እንዲሰጠው ሚኒስቴሩን በተቋሙ ስም የጠየቀበት ማመልከቻ፤

2/ ዝርያውን ያዳቀለው ወይም አግኝቶ ያበለጸገው የመንግስት የምርምር ማእከል ስም፤

3/ በምርምሩ ሂደት የተሳተፉ የመንግስት ተቋም አዳቃዮችና ሌሎች ባለሙያዎች ዝርዝርና በተቋሙ የተቀጠሩ መሆናቸውን የሚያረጋገጥ ማስረጃ፤

4/ ዝርያው በህዝብ ሃብት የፈለቀ ወይም የጎለበተ መሆኑን፤

5/ በዚህ አንቀጽ ን/አንቀጾች 1-4 የተዘረዘሩትን በማረጋገጥ ሚኒስቴሩ ዝርያው የህዝብ ሃብት መሆኑን ጠቅሶ የባለቤትነት መብት የምስክር ወረቀት ለተቋሙ ይሰጠዋል፡፡

8. **ሚኒስቴሩ ለህዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው  በሚከተሉት ሁኔታዎች በአዳቃይ መብት ላይ ገደብ ሊጥል ይችላል፤**

1/ አገር በቀል የዕጽዋት ብዝሃ ሕይወት ሃብት ክምችት ባለበት አካባበቢ እንዳይባዛ በማድረግ፤

2/ የተጠበቀ ዝርያ በሌሎች ዝርያዎች ላይ የሚያስከትለው አሉታዊ ተጽእኖ እስኪታወቅ ድረስ

ሀ/ በተወሰነ ስነምህዳር ውስጥ ብቻ እንዲባዛ በመፍቀድ፤

ለ/ ዝምድና ባላቸው የሰብል ቤተሰብ በሚመረቱበት አካባቢ እንዳይመረት በማድረግ፤

ሐ/ የግለላ ርቀትን መሰረት ያደረገ የአመራረት ሥርዓት እንዲከተል በማድረግ፤

መ/ መብቱ እንዲገደብ ያደረጉት ሁኔታዎች እስኪነሳ ድረስ ፈጽሞ እንዳይመረት ወይም ተመርቶ ከተገኘም እንዳይሸጥ ወይም እንዳይሰራጭ በማድረግ

3/ ጥበቃ የተደረገለትን ዝርያ ዘር ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮለት የተጠቃሚውን ፍላጎት አባዝቶ ለማሟላት ካልቻለ ወይም ለማሟላት ፈቃደኛ ካልሆነ፤

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# በግብርና ሚኒስቴር የወጣ መመሪያ ቁጥር 769/2013

**9. የግዴታ ፈቃድ ለሌላ ወገን ከመሰጠቱ በፊት መንግስት ለህዝብ ጥቅም ሲባል የሚከተሉትን የድጋፍ አማራጮች ለባለመብቱ ሊሰጥ ይችላል፤**

1/ የውጭ ምንዛሬ ግኝትና አጠቃቀምን አስመልክቶ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር፤

2/ የማባዣ ማሳ ተደራሽነት በማረጋገጥ ወይም የኮንትራት ግብርና በአግባቡ በመተግበር፤

3/ ሌሎች አስፈላጊ ድጋፍ እና ግብዓቶች ተደራሽ የሚሆኑበትን ሁኔታ ማመቻቸትን ያጠቃልላል።

**10.በአንቀጽ 8 መሰረት አስፈላጊው ድጋፍ አመቻችቶለት ሚኒስቴሩ መብቱ የተጠበቀ ዝርያ ባለቤት ላይ የግዴታ ፈቃድ ተግባራዊ እንዲሆን ከመወሰኑ በፊት፤**

1/ ለመብት ባለቤቱ ሃሳቡን እንዲገልጽ በጽሁፍ ያሳውቀዋል፤

2/ የዝርያው ባለቤት ከሚኒስቴሩ የተላከለትን የጽሁፍ ማስታወቂያ መሰረት በማድረግ በ15 የስራ ቀናት ውስጥ በጽሁፍ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፤

3/ ሚኒስቴሩ ባለቤቱ ያቀረበውን ምላሽ መሰረት በማድረግ

ሀ/ የተጠቃሚውን ፍላጎት ለሚሟላት ፈቃደኛ ከሆነ የግዴታ ፈቃድን ተግባራዊ አያደርግም፤

ለ/ የተጠቃሚውን ፍላጎት ለሚሟት ፈቃደኛ ካልሆነ ግን የግዴታ ፈቃድን ተግባራዊ ያደርጋል።

**11.ሚኒስቴሩ የግዴታ ፍቃድ ለመስጠት የጠያቂዎችን አመራረጥ በሚከተለው መስፈርት መሰረት ተፈጻሚ ያደርጋል፤**

1/ ጠያቂው በዘር ማምረት የታደሰ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እና የንግድ ፈቃድ ያለው፤

2/ በአገሪቱ የዘር ገበያ ድርሻው ከሌሎች ሲነጻጸር የተሻለ ደረጃ ላይ የሚገኝ

3/ በብቃት ማረጋገጫ አሰጣጥና አስተዳደር መመሪያ መሰረት እና ከዚያም በላይ የሆነ የውስጥ የዘር ጥራት ቁጥጥር ስርዓት የዘረጋ፤

4/ በንጽጽር የተሻለ መጋዘን፣ሎጅስቲክስ /ትራንስፖርት/ እና የሰው ኃይል ያለው

5/ በተጠቃሚዎች እና በሌሎች ባለድርሻ አካላት በተሞላ የእርካታ ግብረ-መልስ ሪፖርት የተሻለ ውጤት ያስመዘገበ፤

6/ የግሉ ይዞታ ያለው ወይም በረጅም ጊዜ የተገባ የማሳ ኮንትራት ውል ያለው፤

7/ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ተጨማሪ መስፈርቶች ማሟላት የሚችል፤

12. ማንኛውም ሰው በአጁ አንቀጽ 17/2 መሰረት የዕጽዋት አዳቃይ መብት ለማግኘት በቀረበ ማመልከቻ ላይ ተቃውሞ በሚከተለው መልኩ ሊያቀርብ ይችላል፤

1/ ተቃወሞ አቅራቢው ማመልከቻወን ሲያቀርብ በኤሌክትሮኒክስ፣ በአካል ወይም በፋክስ በሚቀርብ ማመልከቻ ሊሆን ይችላል፤

2/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የደረሰውን ጥቆማ መነሻ በማድረግ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ለባለመብቱ ያሳውቀዋል፤

3/ ባለመብቱ ከሚኒስቴሩ በደረሰው ጥቆማ መነሻ መሰረት በአስር የሥራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴሩ ምላሽ ይሰጣል፤

4/ ሚኒስቴሩ የቀረበውን መቃወሚያ በህዝብ ጥቅም ላይ የሚያደርስውን ጉዳት

ሀ/ ከሰው፣ ከእንስሳት ወይም ከዕጽዋት ጤንነት፤

ለ/ ከምግብ እና ሥነ ምግብ ዋስትና፤

ሐ/ ከአካባቢ ደህንነት፤

መ/ ከሉዓላዊነት፤ ወይም

ሠ/ የብዝሃ ሕይወት ጥበቃና የአካባቢ ማህበረስብ መብት፤

ረ/ ሌሎች ጉዳዮች ጋር የተያያዘ ስለመሆኑ መርምሮ ለማጣራት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትብብር ይሰራል፡፡

5/ ሚኒስቴሩ የቀረበው መቃወሚያ ዝርያውን በተመለከተ የዕጽዋት አዳቃይ መብት ለመስጠት የሚያስችሉ መስፈርቶችን አለማሟላቱ ጋር የተያያዘ ከሆነ፤

ሀ/ አዲስ መሆኑን ለማረጋገጥ አዋጁ ከፈቀደው የጊዜ ገደብ በላይ ገበያ ላይ ያልዋለ መሆኑን ለማጣራት ልዩ ልዩ ጥናት/ምርመራ ያካሂዳል፤

ለ/ ጥበቃ እንዲደረግለት የቀረበው ዝርያ የተለየ መሆኑን ለማረጋገጥ ተቃዋሚ አቅራቢው ካቀረበው ማመሳከሪያ ጋር ያነጻጽራል፤

ሐ/ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ፍተሻዎችንም ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፤

6/ የቀረበው መቃወሚያ ከባለቤትነት መብት የይገባኛል ጥያቄ ጋር የተያያዘ ከሆነ በተሻለ ባለመብት የሚያደርገውን ማስረጃዎችን ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

7/ ሚኒስቴሩ በቀረበው ተቃወሞ እና በባለብቱ ምላሽ መነሻነት ባደረገው ምርመራ መሰረት የሚከተሉትን ውሳኔዎች ሊሰጥ ይችላል፤

ሀ/ ተቃወሞውን ውድቅ ሊያደርገውና ማመልከቻውን በመቀበል ወደ ቀጣይ የመብት አሰጣጥ ሂደት እንዲተላለፍ ያደርጋል፤ወይም

ለ/ ተቃዎሞ ተቀባይነት የሚኖረው ከሆነ የቀረበውን የዕጽዋት አዳቃይ መብት ጥያቄ ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፤

**13.የዕጽዋት አዳቃይ መብት ከተሰጠ በኋላ ለማሰረዝ የቀረበን ማመልከቻ ለመመርመር እና ውሳኔ ለመስጠት ቀጥሎ በቀረበው ሂደት መሰረት ተግባራዊ ይሆናል፤**

1/ የቀረበው ማመልከቻ ከህዝብ ጥቅም ጉዳት ወይም መስፈርትን ካለሚሟላት ጋር የተያያዘ ከሆነ ማመልከቻውን ለመመርመር ሚኒስቴሩ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ 4 እና 5 የተጠቀሰው ሂደት ይከተላል፤

2/ ዝርያውን ባለማደስ ምክንያት የዕጽዋት አዳቃይ መብት ለማሰረዝ የሚቀርብ ማመልከቻን በሚከተለው መንገድ ይመረምራል፤

ሀ/ ሚኒስቴሩ የዝርያው ባለቤት ስለቀረረበት አቤቱታ በ15 ቀን በጽሁፍ ምላሽ እንዲሰጥ በማድረግ፤

ለ/ ሚኒስቴሩ ከዝርያው ባለቤት በቀረበለት ሪፖርት መሰረት የተጠበቀን ዝርያ ባህርያት ጠብቆ መቆየቱን በመስክ በመገኘት በማረጋገጥ፤

ሐ/ በመስክ የተገኘውን ግብረ መልስ መሰረት በማድረግ ከዝርያው ናሙና ወስዶ በመስክ ወይም በቤተሙከራ ድጋሚ ፍተሻ በማድረግ፤

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ተገቢው ምርመራ ከተከናወነ በኋላ ሚኒስቴሩ የሚሰጠው ውሳኔ ከሚከተሉት አንዱ ሊሆን ይችላል፤

ሀ/ ማመልከቻውን ውድቅ ማድረግና መጀመሪያ የተሰጠውን መብት ማጽናት፤ ወይም

ለ/ በማመልከቻው መሰረት ቀድሞ የተሰጠውን መብት መሰረዝ ብቻ፤ ወይም

ሐ/ በማመልከቻው መሰረት ቀድሞ የተሰጠውን መብት መሰረዝ እና አግባብ ለሆነው አካል ማስተላለፍ፤

**14.የእጽዋት አዳቃይ መብት ለማግኘት ለባህርይ ፍተሻ ተግባር የሚውል ናሙና መጠን ሚኒስቴሩ ለየሰብል ዓይነቴው በሚያዘጋጀው የአሰራር ድንብ መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፤**

15. ጥበቃ የተደረገለትን ዝርያ ዘር ናሙና መጠን፣የቆይታ ጊዜ እና የማከማቻ ዓይነት እና አቀማመጥ በተመለከተ እንደየ ዕጽዋት ዝርያ ዓይነቱ በሚኒስቴሩ የአሰራራ ደንብ /by-law/ ላይ የሚወሰን ይሆናል፡፡

16. ይህ መመሪያ ከየካቲት 19 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**ዑመር ሁሴን**
**ግብርና ሚኒስትር**